# ከእግዚአብሔር ፍቅር

"... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፡፡" (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – glnlm@ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org 1ኛ ደብዳቤ 2006 እአአ 1st Quarter 2006


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡ (ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)

## እስራኤልን የመደገፍ ክርስቲያናዊ ግዴታ

"እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡...እባርክሃለሁ÷ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፡ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ <u>የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡</u>" (ኦሪት ዘፍጥረት 12÷ 2-3)

እነሆ ክርስትናችን የተነሣበት የዕምነታችን ጅማሬና መሠረት ከዚህ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሩቅ አስቦ በተነሣ ጊዜ÷ ዑር የተባለ ሐገር ሰው ÷ አብርሃምን ነበር የጠራው፡፡ እርሱም እግዚአብሔር በተናገረው ጊዜ ሳያቅማማ አመነ፡፡ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት፡፡

የወንጌላችን የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ምን እንደሚል አስተውላችሁ ይሆናል፡፡እንዲህ ይላል "የዳዊት ልጅ÷ <u>የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ</u> ትውልድ መጽሐፍ" (የማቴዎስ ወንጌል 1÷1)

እግዚአብሔር አምላካችን በዚህ ጉዳይ ምንም ጥርጥር እንዳይኖር አስቀድሞ በማሰብ ከአብርሃም እስከ ጌታ ኢየሱስ ድረስ ያለውን የትውልድ ተዋረድ ገልጾልናል፤ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አንድን ስንመለከት ፡- የምድር ነገዶች ሁሉ በረከት ሆኖ የተገለጠው ተስፋችንና ንጉሣችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የአብርሃም ልጅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ አ<u>ብርሃም፡- የይስሐቅ አባት፡- ይስሐቅም የያዕቆብ አባት ሲሆን÷ያዕቆብ ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ አባት ነው</u>፡፡ ይህንን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በመመርመር÷ የሚከተሉትን አራት ፍሬ ነገሮች ማጠቃለል እንችላለን፡፡

1ኛ. እግዚአብሔር አምላካችን የእስራኤልን ሕዝብ በዘላለማዊ ኪዳን መርጦአል፡፡ይኸውም በአብርሃም በኩል የሆነው ጥሪና ምርጫ ነው፡፡

"እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው ፡ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ፡- እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ለበረከትም ሁን፤..."አለው፡፡

*(ዘፍጥረት 12፥1-2)*

ጌታ እግዚአብሔር አምላካችን የዕምነት አባታችንና የእስራኤል አባት የሆነውን አብርሃምን በጠራው ጊዜ ለእርሱና ለልጆቹ (ለእስራኤል) የገባው ቃል ኪዳን የሐገር ውርስም ነበር፡፡



The world book Encyclopedia የተባለ እንሳይክሎፒዲያ፡- ኢየሱስ ክርስቶስን በገለጸበት መዝገብ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ÷የክርስትና ዕምነት መስራች÷ ሲል ያሰቀመጠው ምስል

መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- "በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳን አደረገ፡ <u>ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ</u> ይህችን ምድር <u>ለዘርህ</u> ሰጥቼአለሁ" ይልና ÷ ሥፍራውንም ሲያረጋግጥ "... ከነዓናውያንንም÷ጌርጌሳውያንንም፡ ኢያቡሳውያንንም፡" በማለት በውርሱ ውስጥ የሚጠቃለሉትን ሐገሮች ይገልጻል፤ ስሙ ብሩክ ይሁን፡፡ (ዘፍጥረት 15÷18-21)

ከዚህ የምንረዳው እስራኤል የአምላካችን የኪዳን ሐገርና ሕዝብ ስለሆነች÷ማንም ሊቀናባትና ሊመቀኝባት የማይገባ ÷ <u>ለምድር ነገዶች ሁሉ በረከት፡ መነሻ ሆና እንደተመረጠች</u> ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ እንደሚያሳየው÷ሕዝቦች <u>እንዲባርኳት</u>ና እንዲባረኩባት ታስባ የተመረጠች የእግዚአብሔር ሥራ ማዕከል ናት፤ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

"የሚባርኩህንም እባርካለሁ÷ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ፡፡" (ዘፍጥረት 12÷3)

ወገኖቼ፡- የእግዚአብሔር ቃል የማይሻርና÷የታመነ ነው፡፡ ጌታ እግዚአብሔር የርስቱ መያዣና የመንግሥቱ ጥንስስ የሆነውን ያዕቆብን (እስራኤልን) "ከበበው ተጠነቀቀለትም፤ እንደ ዐይን ብሌን ጠበቀው" እንደሚል ከግብፁ ፈርዖን እስከ ፔርሺያዊው ሓማ÷እንዲሁም እስከ አዶልፍ፡ ሂትሌር ድረስ÷የሕዝቡን ጠላቶች ሲበቀል ታይቶአል፡ክብር ለስሙ ይሁን፡፡ (ዘዳግም 32÷ 10)

2ኛ.የሰው ልጆች ታላቁ በረከት የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእራኤል ዘር ÷ የዳዊት ልጅ ነው፡፡

እግዚአብሔር አምላክ አብርሃምን የጠራባት ያቺ ቀን ለዘላለም የተባረከች ናት፡፡አብርሃምም አስቀድሞ ያላወቀውን ሕያው አምላክ ቃል አምኖ÷ወደማያውቀው ምድር በመሄዱ ብሩክ ነው ስለዚህ ዘሩም ለዘላለም ብሩክ ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 4÷22 "እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤እኛ (ግን) <u>መዳን ከአይሁድ ነውና</u>÷ ለምናውቀው እንሰግዳለን" ያለው ሁልጊዜ ሐሳቤን ይጠብቅልኛል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስም ስለ ሕዝበ እስራኤል እንዳንሳሳት እንደሚከተለው መክሮናል፡፡

"ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ÷ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ÷ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ÷ <u>በቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤ ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም</u>፡፡"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 11÷17-18)

እንዲያውም ቃሉ ሲያስጠነቅቀን "ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ" ይላል፡፡

(ሮሜ 11÷20)

እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ሁሉ÷ ስለ እስራኤል እንዳይሳሳት መጽሐፍ ቅዱሳችን በሰፊው ያስተምረናል፤ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእስራኤል ጋር የተሳሰረ ስለ ሆነ÷ክርስቲያን ሆኖ÷ እስራ

ኤልን አለመደገፍ የሚጋጭና፥ ግራ ነው፡፡ ርጉምም ነው፡፡ እስቲ ትንቢተ ኢሳይያስን እንመልከት "በዘመኑ ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል ፥ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል፥አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ፡፡ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከእየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ ሄደው፡ ኑ ወደ እግዚአ ብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ፡፡"

(ትንቢተ ኢሳይያስ 2፥2-3)

ይህ የእግዚአብሔር እስራኤልን መምረጥ የማበላለጥ ሀሳብ ሳይሆን ለምድር ሁሉ መድኃኒት መሆኑ በትንቢት እንዲህ ተጽፏል፡፡

"የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ፡ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመልስ፡... እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ፡፡" (ትንቢተ ኢሳይያስ 49፥6)

3ኛ. እየሩሳሌም የምንጠባበቀው የእግዚአብሔር የጽድቅ መንግሥት ማዕከል ናት፡፡

እግዚአብሔር ለነቢዩ ሕዝቅኤል ያሳየው የሚመጣው የእየሩሳሌም መልክና አሠራር እጅግ ይደንቃል፡፡በትንቢተ ሕዝቅኤል 40 ላይ፥ ጉልበት ሁሉ ለጌታችን የሚሰግድበትን መቅደስ አስደናቂነት ማሰብ እንድንችል፥አስቀድሞ የተሰጠንን ማንበብ ይቻላል፡፡

መዝሙረ ዳዊት ደግሞ "በሰሜን ወገን በመልካም ሥፍራ የቆመ የምድር ሁሉ ደስታ የጽዮን ተራራ ነው፤ እርሱም የታልቁ ንጉሥ (የእየሱስ ክርቶስ) ከተማ ነው፡፡" ይላል፡፡ (መዝሙረ ዳዊት 48፥2)

4ኛ. እስራኤልን መባረክ ይባርካል፡፡

መጽሐፍ እንዲህ ይላል "ኢየሩሳሌም ሆይ፤እግሮቻችን ከደጆችሽ ውስጥ ቆመዋል፡፡ ኢየሩሳሌም እጅግ እንደ ተጠጋጋች ከተማ ሆና ተሠርታለች፡፡ ለእስራኤል በተሰጠው ሥርዓት መሠረት፥ የእግዚአብሔርን ስም ለማመስገን የእግዚአብሔር ነገዶች፥ወደዚያ ይመጣሉ፡፡ በዚያም የፍርድ ዙፋኖች የሆኑት የዳዊት ቤት ፥ ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀሮቼ፥ በውስጥሽ ሰላም ይስፈን እላለሁ፡፡ ስለ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት በጎነትሽን እሻለሁ፡፡

(መዝሙረ ዳዊት 122 አ/መ/ት/)

ውድ ወገኖች፡- በአዲስ ኪዳን ደግሞ እንዲያውም ከቀድሞው ይበልጥ ጠንከር ያለ ትዕዛዝ እና ያለን፤ እንዲህ ተጽፎአል፡፡ "... አሕዛብ የአይሁድ መንፈሳዊ በረከት ተካፋዮች ከሆኑ፥ያገኙትን ምድራዊ በረከት ከአይሁድ ጋር ይካፈሉ ዘንድ የእነርሱ ባለ ዕዳዎች ናቸው፡፡"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 15፥27 አ/መ/ት)

ደግሞም፡- "ስለ ቤተ መቅደሱ ይበቀላል፡፡... ጥበቃውን አጠንክሩ፤ዘብ ጠባቂውን አቁሙ፤ደፈጣ ተዋጊዎችን አዘጋጁ!" እያለ ከእስራኤል ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን፥ ስለ አምላካችን ፈቃድ መቆም እንደሚገባን ያዝዘናል፡፡ አንሳት፥ ትዕዛዙ ለጥቅማችን ነው፡፡



በዕብራይስጥ አሊያሕ የተባለው የአይሁድ ወደ እስራኤል መመለስ፥የተሰፋው ቃል ፍጻሜ ነው

የእስራኤል ምርጫ የምድር ነገዶች ሁሉ በረከት እንጂ አድልኦ አይደለም፡፡ ስለዚህ ቅዱሳን ሁሉ የሚደግፏት ሲሆን በምቀኝነት የሚቃወሟት የአመጻና የጥፋት ልጆች ናቸው፡፡ ስለዚህ በልጁ በ ኢየሱስ በማመን የአብርሃሙ ምርጫና ጥሪ ተቀጥያዎች የሆንን ክርስቲያኖች ያለማወላወል ከወንድሞቻችን ከእስራኤል ሕዝብ ጋር መቆማችን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሆኑን እናውቃለን፡፡

በመጨረሻ መታሰብ ያለበት ነገር፥ የምንጠባበቀው ንጉሣችን የጌታ የእየሱስ ክርስቶስ መናገሻ እየሩሳሊም መሆኗን ነው።

ይህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ካለልን፥ እኛ ክርስቲያኖች እስራኤልን የምንደግፈው እንዴት ነው?

1ኛ. ሕዝቡ ከተበተነበት ከዓለም ሐገሮች ተመልሶ በሐገሩ ለመቋቋም በሚያደርገው ጥረት መርዳት፡፡

ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤አሕዛብን በጥቀሻ እጠራለሁ፤ ዓርማዬንም ለሕዝቦች ከፍ አደርጋለሁ፤ ወንዶች ልጆችሽን በዕቅፋቸው ያመጡልሻል፤ሴቶች ልጆችሽንም በትክሻቸው ይሸከሙልሻል፡፡"

(ትንቢተ ኢሳይያስ 49፥22)

እንዲሁም "ለመንግሥታት ምልክትን ያቆማል፤ ከእስራኤልም የተሰደዱትን መልሶ ያመጣቸዋል የተበተኑትን የይሁዳ ሕዝብ ከአራቱ የምድር ማዕዘን ይሰበስባል፡፡" (ትንቢተ ኢሳይያስ 11፥12)

2ኛ. በቁሳዊና በሞራል አስተዋጽኦ መደገፍ፡-

አበው "ዓርብ ዓርብ ይሸበራል እየሩሳሌም" እንዳሉት፡ አሸባሪዎችን እየተቋቋመች በመታደስ ላይ ያለችውን እስራኤልን በሞራልና በቁሳዊ አስተዋጽኦ መርዳት ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ቃሉ እንዲህ ይላል፡-

"አጽናኑ፤ሕዝቤን አጽናኑ፤ይላል አምላካችሁ፡፡ ለእየሩሳሌም አለዝባችሁ ንገሯት ፤ ዐውጁላትም፤ በባርነት ያገለገለችበት ዘመን አብቅቶአል፤የኃጢአቷም ዋጋ ተከፍሎአል ፤ ስለ ኃጢአቷ ሁሉ ከእግዝአብሔር እጅ ሁለት እጥፍ ተቀብላለች፡፡"

(ትንቢተ ኢሳይያስ 40፥1-2)



ወደ ምድራችው የተመለሱ የኢትዮጵያ አይሁድ ልጆች በአንድ የእየሩሳሌም መዋዕለ ሕፃናት

3. በጸሎት መደገፍ፡-

"እንዲህ ብላችሁ ለኢየሩሳሌም ጸልዩ፤የሚወዱሽ ይለምልሙ፤ በቅጥርሽ ውስጥ ሰላም ይሁን፤በምሽግሽም ውስጥ መረጋጋት ይስፈን፡፡" (መዝሙረ ዳዊት 122፥6-7 አ/መ/ት/)

አሜን? አሜን፡፡ ተባረኩ፡፡

# ከሁሉ የከፋ ችግር

በአንድ የሩቅ ምሥራቅ ሐገር ኗሪ፥ አንድ ጠቢብና አስተዋይ ሽማግሌ ነበር፡፡የሐገሬውም ሕዝብ ግራ የገባቸውን ማንኛውም የዕለት ጥያቄአቸውን ወደ እርሱ ይወስዱ ነበር፡፡ እርሱም ይፈታላቸው ነበር፡፡ ስለዚህ በሐገሬው ሕዝብ ዘንድ ታላቅ አክብሮትና ተወዳጅነት ነበረው ይባላል፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን፥ከሐገሬው ሕዝብ አንዱ ገበሬ፥እየታወከ፥ወደ ሽማግሌው መጣና፡- "ጠቢቡ! እጅግ አሰቃቂ ነገር ደርሶብኛል፡ በሬዬ ሞቶብኛል፡፡ አርሼ ቤተሰቤን የማሳድርበት ሌላ በሬ የለኝም፡፡ ከዚህም የከፋ ችግር ፈጽሞ ያለ አይመስለኝም፡፡ አንተስ ምን ትላለህ?"ሲል ጥያቄውን አቀረበ ጠቢቡም ሽማግሌ፡- እንደ ልማዱ ረጋ እያለ፡-"ሊሆንም ላይሆንም ይችላል" ሲል መለሰለት፡፡ በዚህ ጊዜ በሽማግሌው መልስ ያልረካው ገበሬ እየተቈጣ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ በሠፈሩም እየተ

ዘዋወረ፥"ጠቢቡ ሰው አብዶአል ጥያቄዬን መመለስ አልቻለም፥ የበሬዬ መጥፋት ከችግር ሁሉ የከፋ መሆኑን አላወቀም፥ እያለ ማስወራት ጀመረ::

በነጋታው ግን ገበሬው እንደ ልማዱ ማልዶ ተነሥቶ በሩን ከፍቶ ወጣ ሲል፦ አንድ እጅግ ብርቱና ጤነኛ የሆነ (ባለቤት ያልነበረው) ፈረስ፥ በማሣው ውስጥ ሲዘዋወር አገኘ:: ገበሬውም በጠፋው በሬው ፈንታ ፈረሱን ይዞ መጠቀም እንድሚችል በልቡ መጣለት:: ፈረሱንም ይዞት ያርስበት ጀመር:: ፈረሱም ከጠፋው በሬ ይበልጥ ለእርሻ ያመቸ ስለ ሆነለት በጣም ተደሰተ::

ሐዘኑ ወደ ታላቅ ደስታ የተለወጠለትም ገበሬ ፥ የገጠመውን አስደሳች ነገር ለጠቢቡ ሰው ገልጦ ይቅርታ ለመጠየቅ ተመልሶ ሄደ:: በደረሰም ጊዜ ፦ "ጠቢቡ! ቃልህን ስላላመንሁ ይቅርታ እለምንሃለሁ:: በበሬዬ መጥፋት፥ ከሁሉ የከፋ ችግር የደረሰብኝ መስሎኝ ነበር:: ያንተንም ቃል መስማት አልቻልሁም ነበር:: ነገር ግን ዕውነትህን ነበር:: ችግሬ ከሁሉ የከፋ አልነበረም:: እንዲያውም ለመልካም ሆነልኝ:: በሬዬ ባይጠፋ ኖሮ፥ይህንን የመሰለ ፈረስ ባላገኘሁ ነበር:: ስለዚህ በበሬዬ መጥፋት ከሁሉ የተሻለ ነገር የደረሰኝ ይመስለኛል::አንተስ ምን ይመስልሃል?" ሲል ሌላ ጥያቄ አቀረበለት:: ጠቢቡ ሰው ግን አሁንም እንደ ቀድሞው "ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፦" ሲል መለሰለት:: በዚህን ጊዜ ገበሬው እንደገና በቁጣ ተሞላና "አሁንስ በእርግጥ አብደሃል" አለው:: እየተቆጣም ወደ መንደሩ ተመለሰ::

ግራ የተጋባውም ገበሬ፥ ጠቢቡ የተናገረው ብዙውን ጊዜ ስለሚፈጸም ፥ ከዚህ በኋላ ደግሞ ምን ይመጣ ይሆን እያለ ቀናት አለፉ:: ይህ በእንዲህ እንዳለ፥አንድ ቀን የገበሬው ልጅ ፈረሱን ሲጋልብ ወድቆ እግሩን ተሰበረ::እጅግም ስለ ተጎዳ አባቱን ሊረዳ የማይችል ሆነ:: በነገር ሁሉ ቶሎ የሚማረረውም ገበሬ "ወየው! ወየው ልጄ! አሁንስ ልጄ ከተሰበረ፥ መከሬን ለመሰብሰብ የሚረዳኝ የለኝም:: ወየው! እንግዲህ ልንራብ ነው:: ከዚህም የከፋ ችግር የለም" እያለ ደግሞ ሌላ ጥያቄውን ለማቅረብ ወደ ጠቢቡ ሰው ቤት ገሰገሰ::

ገበሬውም ፥ ጠቢቡ ሽማግሌ ቤት እንደ ደረሰ፦ እንዲህ መቀባዠሩን ጀመረ:: "ለመሆኑ ጠቢቡ፦ፈረሱን ማግኘቴ ከሁሉ የተሻለ ነገር እንዳልነበረ እንዴት አወቅህ? ይኸውልህ፥ልጄ ከፈረሱ ወድቆ ተሰብሯል:: ጊዜው የመከር ጊዜ ነው:: መከሩን መሰብሰብ የሚረዳኝ የለኝም ::ይኸው እንግዲህ ምንም የማይተካከለው መከራ መጣብኝ:: አሁንስ ከዚህ የከፋ ችግር ሊኖር አይችልም:: አንተም ከእኔ ጋር እንደምትስማማ አልጠራጠርም::"በማለት በረዥሙ ተነፈሰና መልሱን ይጠባበቅ ጀመረ:: በዚህን ጊዜ ጠቢቡ ሽማግሌ፥በርጋታና በርኅራኄ ገበሬውን ቀና ብሎ ተመለከተና "ልጄ ሆይ! ሊሆንም ላይሆንም ይችላል" ሲል መለሰለት:: ገበሬውም በቍጣ ተሞልቶ፥ይህ ሰው ደንቆሮ እንጂ ጠቢብ ሊባል አይገባውም እያለ እያጕረመረመ ወደ ቤቱ አመራ::

በነጋታው የሐገሩ የጦር ሠራዊት ወታደሮች በየመንደሩ እየተዘዋወሩ ለአቅም የደረሰውን ወጣት ሁሉ እያፈሱ ወደ ገበሬው ቤት ደረሱ:: በወቅቱ ጦርነት ስለ ነበረ ወታደራዊ ግዳጅ ነበር:: ወታደሮቹም የገበሬውን ልጅ ሲመለከቱት፡ ከፈረስ ወድቆ ተሰብሮ ስለ ነበረ ሊወስዱት አልቻሉም:: በዚያም ምክንያት የሠፈሩ ወጣቶች ወደ ጦር ዘምተው ሲሞቱ የገበሬው ልጅ ግን በሕይወት ተረፈ ይባላል:: (አንባቢ ያስተውል) የልጁ ከፈረስ ወድቆ መሰበር በጊዜው በጣም ቢያሳዝንም፥ የሕይወቱ መትረፊያ ምክንያት ሆኖ ተገኘ::

የዚህ ታሪክ ፍሬ ነገር እጅግ ኃይለኛ ነው:: ብዙዎቻችን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሳናልፍ አልቀረንም:: የምናልፍበት ችግር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሁሉ የከፋ ይመስለናል:: ችግራችንን ከፍ አድርገን በማየት መጨነቅ ይቀልለናል:: የማይመቸን ሁኔታ ሲያጋጥመን፥ ሊገድለንና ሊያጠፋን ብቻ የመጣብን ይመስለናል:: ዕውነቱ ግን አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ አይደለም::

የዚህ መልዕክት አዘጋጅ ከሃያ ሁለት ዓመታት በፊት የዚህን ገበሬ ታሪክ በመሰለ ልምምድ ውስጥ አልፍ ነበር::ከዚያ ቀደም ሲል፥ የልጅነት ራዕዬንና ተስፋዬን ሁሉ ትቼ የተከተልሁት ነገር ነበር:: ያም ብዙ መስዋዕት የተከፈለበት ነገር በፍጹም ባልተጠበቀ አኳኋን እንደማይነካ ሆኖ ተንኰታኰተ:: እኔም ቅስሙ እንደ ተሰበረበት ሰው ሁሉ፥መቆም ተሳነኝ:: ወጣት ስለ ነበርሁ እንደምንም ተንገዳግጄ ለመቋቋምና ለመኖር ሞከርሁ:: ተስፋ የመቁረጥ ጨለማ ነገሩን ፥ ከሁሉ የከፋ ችግር የደረሰብኝ አድርጎ አሳየኝ:: ስለዚህም ሕይወት ዋጋ የለውም፥ሞት ይሻላል፥ወደ ማለት ደረስሁ::ሞትንም በብርቱ ፈለግሁ:: ለጊዜው ግን ሞትም ሆነ ሕይወት የሚገኝ አልመስለም:: በዚያ ሁኔታ ውስጥ ነበር፤ የጌታዬን የእየሱስ ክርስቶስን የምሕረት እጆች ተዘርግተውልኝ ሰምቼ የወደቅሁባቸው:: በዚያም አስቃቂ ሁኔታ ውስጥ የዘላለምን ሕይወት የሚያክል ታላቅና ዘላለማዊ ትሩፋት አገኘሁ:: ያቺንም የጻግማዊ ልደቴን ዕለት ለዘላለም እባርካታለሁ:: ያም ከሁሉ የከፋ ጨለማዬ ፥ ወደሚደነቀው የደኅንነት ብርሃን መሻገሪያዬ ሆነኝ:: "ያስጨነቅኸኝ ለመልካም ሆነልኝ" እንደ ተባለውም ሆነልኝ:: እግዚአብሔር ይመስገን:: ከሁሉ የከፋ ችግር የደረሰብህ ይመስልሃል? አይዞህ:: ጽና::

"እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን::"
ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥28

## "በጎነትን አደርግ ዘንድ አስቤአለሁ አትፍሩ"

እግዚአብሔር አምላካችን ለሰው ሁሉ ያለውን ፍቅሩን ለመግለጽ ደኅንነትን በእስራስራኤል እንደ ጀመረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል:: ሕዝበ እስራኤልም በአመጸኛነት አምላኩን እግዚአብሔርን ያስቆጣና ያስመርር ነበር:: በዚህ ዘመን ቀስ በቀስ የእግዚአብሔር ክብር እየተዘነጋ እንዳለ ሁሉ በዚያም ዘመን የጌታ ክብር ከእስራኤል ተለይቶ፥መቅደሱም ፈርሶ ነበር:: ኢካቦት እንደተባለው ማለት ነው:: ከአንድ ግለሰብ ሆነ ከሕዝብ የእግዚአብሔር ክብር ሲለይ ከማየት የከፋ ምንም ነገር የለም:: በቶሎ ንስሐ ያልገቡበት ኃጢአት በእርግጥ የጌታን ክብር ያርቃልና:: የሚከተለው እስራኤል ለውድቀት የደረሰበትን መንገድ የሚያሳይ ነው::

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሮአል፦ እውነተኛውን ፍርድ ፍረዱ ፤ ቸርነትንና ምሕረትን ሁላችሁ ለወንድሞቻችሁ አድርጉ፤መበለቲቱንና ድሀ አደጉን፣ መጻተኛውንና ችግረኛውን አትበድሉ ፤ ከእናንተም ማንም በወንድሙ ላይ ክፉውን ነገር በልቡ አያስብ።" ይልና"<u>እነርሱ ግን...መስማትን እምቢ አሉ፤...እግዚአብሔር በቀደሙት ነብያት እጅ በመንፈሱ የላከውን ሕጉንና ቃሉን እንዳይሰሙ ልባቸውን እንደ አልማዝ አጠነከሩ፤ ስለዚህ ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ቁጣ መጣ።</u>" ይላል።
*(ትንቢተ ዘካርያስ 7፥ 9-12)*

*እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ በኃጢአት ላይ ይፈርዳል፡ ከዚያም አንደ መልካም አባትነቱ መልሶ ያቋቁማል። እየሩሳሌም ከቁጣም ሆነ ከበረከት በፊት ማስጠንቀቀያ ተሰጥቶአታል። ለሁለቱም የዝግጅት ጊዜ ነበረ። ሁለቱንም ለመቀበል ሆነ ላለ*

መቀበል ሰው ምርጫ አለው። ም
ክንያቱም እግዚአብሔር ጻድቅ አ
ምላክ ስለሆነና ሰው ወደ በረከት
ይፈጥን ዘንድ ወይም ከእርግማን ይ
ሸሽ ዘንድ ስለሚያስጠነቅቅ ነው።
የሚከተለው በእስራኤል ላይ የወረ
ደው ቁጣ ከተፈጸመ በኋላ የተሰጠ
መልሶ የማቋቋም ተስፋ ነው።

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እ
ንዲህ ይላል፡-መቀደሱ ይሠራ ዘንድ
የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ቤት
ከተመሠረተበት ቀን ጀምሮ ከነቢያ
ት አፍ ይህን ቃል በዚያ ዘመን የሰ
ማችሁ እናንተ ሆይ፥ እጃችሁን አበ
ርቱ። ከዚያ ወራት አስቀድሞ ለሰ
ውና ለእንስሳ ዋጋ አልነበረምና፡ እኔ
ም ሰውን ሁሉ በወንድሙ ላይ አስ
ነስቼ ነበርና፡ ከአስጨናቂው የተነሣ፡
ለሚገባውና ለሚወጣው ሰላም አ
ልነበረም። አሁን ግን እንደ ቀደመው
ዘመን በዚህ ሕዝብ ቅሬታ ላይ አል
ሆንም፥ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአ
ብሔር። ነገር ግን ሰላምን እዘራለሁ፥
ወይኑ ፍሬውን ይሰጣል፥ምድርም አ
ዝመራዋን ታወጣለች፥ሰማያትም ጠ
ላቸውን ይሰጣሉ። ለዚህም ሕዝብ
ቅሬታ ይህን ነገር ሁሉ አወርሳለሁ።
የይሁዳ ቤትና የእስራኤል ቤት ሆ
ይ፥ በአሕዛብ ዘንድ እርግማን እንደ
ነበራችሁ፥እንዲሁ አድናችኋለሁ፥ በረ
ከትም ትሆናላችሁ፥አትፍሩ፥እጃችሁ
ን አበርቱ። ... አባቶቻችሁ እጅግ
ባስቈጡኝ ጊዜ ክፉ ለማድረግ እንዳ
ሰብሁ፥ እንዳልተጸጸትሁም ... እንዲ
ሁ ዳግመኛ ለእየሩሳሌምና ለይሁዳ
ቤት በዚህ ወራት በጎነትን አደርግ
ዘንድ አስቤአለሁ፡(እና) አትፍሩ፡"

(ዳሩ ግን ያሰብሁላችሁን በጎነት ለመ
ቀበል) "የምትሠሩት ነገር ይህ ነው፤
እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራው ጋር እ
ውነትን ተነጋገሩ፡ በበር አደባባያችሁ
ም የእውነትንና የሰላምን ፍርድ ፍ
ረዱ፤ ሁላችሁም በባልንጀራችሁ ላይ
ክፉን ነገር በልባችሁ አታስቡ፡የሐሰት
ንም መሐላ አትውደዱ ፣ ይህን ነገር
ሁሉ እጠላለሁና ፣ ይላል እግዚአ
ብሔር።"(ትንቢተ ዘካርያስ 8፥ 9-18)

ወገኖች፡- በዚህም ዘመን መንፈስ
ለአብያተ ክርስቲያናት፡-
"በዚህ ወራት በጎነትን አደርግ ዘንድ
አስቤአለሁ (እና) አትፍሩ።"ይላል።
ይህም ማለት የእግዚአብሔርን መ
ቅደስ መሥራት ለሚፈልጉ (የወንጌ
ል መልክተኞች) የሚያስፈልግ የጌታ
ረድዔት ማለት ነው። ለመሥራት
እጅግ አመች ጊዜ አለ። አብዛኛው
ን ጊዜ ግን ከተቃዋሚው የተነሣ፥
የጌታ ሥራ እጥፍ ይከብዳል። ቢሆን
ም እግዚአብሔር በዓለም አቀፍ ደ
ረጃ የመንግሥቱን ጠላቶች በማዳከ
ም የራሱን ሠራተኞች ክንድ ለማበ
ርታት የተነሣበት፡- ይህ ዘመን የተባ
ረከ የሥራ ጊዜ ነው።

በትንቢት ቃል መሠረት በእየሩሳ
ሌም መቀደሱ እንደገና ሊሠራ እን
ዳለው እናውቃለን። የወንጌል ሠራ
ተኞች የምንሠራው መቀደስ ግን ሥ
ጋ ለባሹን ሁሉ፡ ወደ ፈጣሪው መጋ
በዝና ሕያው የእግዚአብሔር ማደ
ሪያ፥ ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው።
የቀደሙት ክርስቲያኖች እስከ ሞት
ተግተው፥ በማይመቹ ሁኔታዎች ውስ
ጥ ወንጌልን ሰበኩ። በአንዳንድ ወቀ
ቶች ደግሞ ያለ ብዙ ድካም ብዙ
ነፍሳትን ወደ ጌታ መንግሥት ማፍለ
ስ ተችሎአል።

በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያንን፡ አይታው በማታውቀው
የፍሬ መጠን ሊባርካት አስቦአል።
በድፍረት ኢየሱስ ያድናል ፥ ብሎ
ለመመስከር ከዚህ የተሻለ ዘመን
መልሶ ላይገኝ ይችላል። ሌላው ቀ
ርቶ በማያምኑት ፊት ኢየሱስ ጌ
ታ ነው ማለት የማይቻልበት ዘመን
እንኳ ሩቅ ላይሆን ስለሚችል ጊዜ
ውን መዋጀት ያሻል።

የወንጌልን ሥራ ያለ እግዚአብሔር
መንፈስ እርዳታ መሥራትና ፍሬያማ
መሆን እንደማይቻል እናውቃለን።
እርሱ ግን ቅዱስ ስለ ሆነ ንስሐ በሌ
ለበት ተገኝቶ ለማገዝ አይችልም።
በዘመናችን ብዙ ምዕመናን የሚገባ
ቸውን ፍሬ ሳያዩ ዓመታት ከሚቆጥ
ሩባቸው ምክንያቶች ይህ አንዱ ነው
ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በበዓለ ሃምሳ
ም ቀን ፥ ዛሬም ፥ ለዘላለምም ያው
ነው። ማዳኑ አልተለወጠም፤ክብሩ ይ
ስፋ።

በትንቢተ ዘካርያስ 8፥15 "...በዚህ
ወራት በጎነትን አደርግ ዘንድ አስቤ
አለሁ (እና) አትፍሩ" ያለው ታላቅ
የተስፋ ቃል ፥ የሚፈጸምበት ሁኔታ
ከዚያው ቀጥሎ ባለው ዐረፍተ ነገር
ተመልክቶአል። እንዲህ ይላል።

"እናንተ ልታደርጉት የሚገባ ነገር
ይህ ነው፤ እርስ በርሳችሁ እውነት ተ
ነጋገሩ። በፍርድ ሸንጎዎቻችሁ ሰላም
የሚገኝበትን እውነተኛ ፍርድ ስጡ፡
እርስ በርሳችሁ ለመጎዳዳት ፤ አንዱ
በሌላው ላይ ተንኮል አያስብ፤ምላች
ሁ በሐሰት አትመስክሩ፤ እኔ ሐሰትን
ና ግፍን ሁሉ የምጠላ አምላክ ነኝ"
(ትቢተ ዘካርያስ 8፥16-17 አዲሱ ርጉምት)

ከጌታ መገለጥ በፊት ለክርስቲያን
ሊደረግ የሚችል፥ ከሁሉም የሚበል
ጥ የእግዚአብሔር በጎነት አለ።ይኸ
ውም ፍሬያማነትና የሕይወት ስኬት
ነው። እርሱን በመፍራት የሚገኝ
የእግዚአብሔር በጎነት የሕዝቡን ል
ብ ወደ አምላኩ ይመልሳል። ያም
የሕዝቡን ሕይወት ፍሬያማ ያደርጋ
ል። የክርስቲያን ፍሬያማነት ደግሞ
የእግዚአብሔር ክብር ነው፡ "ብዙ
ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብት
ሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል"
(የዮሐንስ ወንጌል 15፥ 8)

ውድ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ፡-
አምላካችን "በጐነትን አደርግ ዘንድ
አስቤአለሁና አትፍሩ" ብሏል። ነገር
ግን ለበረከት የምንመች ሆነን መገኘ
ት ይኖርብናል። በቤተ ሰብ፥ በቤተ
ክርስቲያንና ፥ በማሕበረ ሰብ ዕውነ
ተኛነትና ጽድቅ መጠበቅ አለባቸ
ው። በምሕረትና በርኅራኄ ራሳችንን
ለበረከቱ ማዘጋጀት አለብን።ካልሆነ
ግን የሕዝቡ ረዳት የሆነውን መንፈ
ሱን እያሳዘንን በጐነቱ ወደ እኛ እን
ዴት ይለፍ?

"... በዚህ ወራት በጎነትን አደርግ
ዘንድ አስቤአለሁ (እና) አትፍሩ፡"
ነገር ግን፡-"የሠራዊት ጌታ እግዚአ
ብሔር እንዲህ ብሎ ተናግሮአል፡
እውነተኛውን ፍርድ ፍረዱ፤ቸርነትን
ና ምሕረትን ሁላችሁ ለወንድሞቻ
ችሁ አድርጉ ፤ መበለቲቱንና ድሀ
አደጉን ፥ መጻተኛውንና ችግረኛውን
አትበድሉ፤ ከእናንተም ማንም በወን
ድሙ ላይ ክፉውን ነገር በልቡ አያ
ስብ።" "የምትሠሩት ነገር ይህ ነው፤
እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራው ጋር እ
ውነትን ተነጋገሩ፡ በበር አደባባያችሁ
ም የእውነትንና፡የሰላምን ፍርድ ፍረ
ዱ፤ሁላችሁም፡በባልንጀራችሁ ላይ ክ
ፉን ነገር በልባችሁ አታስቡ፡የሐሰትን
ም መሐላ አትውደዱ፡ይህን ነገር ሁ
ሉ እጠላለሁና፡ይላል እግዚአብሔር"
(ትንቢተ ዘካሪያስ 7፥9 እና 8፥ 16-17)

የእግዚአብሔር በጎነት እርሱም ለ
መንግሥቱ ሥራ የሚያስፈልገው ጸጋ
ፈጥኖ ይብዛልን። አሜን።

# ከእግዚአብሔር ፍቀር የደብዳቤ አገልግሎት

እግዚአብሔር በሰጠን በዚህ አገልግ
ሎት እየተጋን፥ በሚመችና በማይመ
ች ሁኔታ ውስጥ አልፈን፡ እነሆ ስድ
ስት ዓመት በጸጋው ሞላን። በዚህ
ም የጠራንን ጌታ ታማኝነት እናደን
ቃለን። ሆኖም ከመንፈቀ ያህል ወዲ
ህ፡ የገቢ ምንጫችን የነበረው ለጊ
ዜው እንደ ተቋረጠ፥የሰማችሁ ቅዱ
ሳን ፥ በሚያስደንቅ ፍቅራችሁ ከእኛ
ጋር ስለቆማችሁ ጌታን እናመሰግና
ለን። ጌታዩ ኢየሱስ ይክፈላችሁ።

## ጌታ ይባርካችሁ

1. ፓስተር ደባልቄና ትርሲት ያረጋል
(አማኑኤል ቤተክርስቲያን÷ ካንሳስ)

2. ወንድም ረድዔት ኤዴሳ

(ስፕሪንግ ፊልድ÷ ሙዙሪ)

3. ዶ/ር ሚካኤልና ጥሩ ዓለም በለጠ

(ሚልዋኪ÷ ዊስኮንሲን )

4. እህት ዓለም ዘርዓይ
(ሴንት ሉዊስ÷ ሙዙሪ)

5. ወንድም ዘሪሁን ቀነዓ
(ካንሳስ ሲቲ÷ ሙዙሪ)

6. ወንድም ሰለሞን አንበርብር
(ካሊፎርኒያ)

7. እህት ቀበኔና ፓስተር ጌታቸው በየነ
(ሲያትል÷ ዋሽንግተን)

8. እህት አሰለፈችና ዶ/ር ደበበ
ገብረ መድኅን (ሚልዋኪ፤ዊስኮንስን)

ኢየሱስ ጌታ ነው።
ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።

## መንግሥተ ሰማይ ? .

ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት፡እውነት
እልሃለሁ÷ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ
በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት
ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆድሞስ
ም ፡- ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት
ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እ
ናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ
ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለ
ሰ÷ እንዲህ ሲል፡- እውነት፡ አውነት
እልሃለሁ ÷ ሰው ከውኃና ከመንፈስ
ካልተወለደ በቀር ፡ ወደ እግዚአ
ብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም
የዮሐ ወንጌል 3÷3-5

አማን፡አማን፡እብለካ፡ዘኢተወልደ፡ዳ
ግመ፡ኢይክል፡ርእይዮታ፡ለመንግሥ
ተ፡እግዚአብሔር።ወንጌል፡ዘዮሐንስ፡
ም ፫፤፫ (ግዕዝ÷ሐዲስ፡ ኪዳን)

"ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር"?

ኢየሱሰ ጌታ ነው፤ጌታ ይባርካችሁ።